
የእስልምና መሰረቶች

አንደኛ ክፍል



በሳፊያ ኢቅባል

ትርጉም በአህመድ የሱፍ



የአማርኛ እትም

- የወጣቱ ተልዕኮ
- ኢሜል፡ ahmedyesuf29@gmail.com
- ዌብሳይት፡ www.youth-mission.com

የእስልምና መሰረቶች

የእስልምና ጥናቶች የመማሪያ መጽሐፍ

አንደኛ ክፍል



በሳፊያኢቅባል

MA, MA, B,Ed

ትርጉም በአህመድ የሱፍ

© አል-አስር ህትመት

በዚሁ ደራሲ የተዘጋጁ ሌሎች መጽሐፍት፡-

- የእንግሊዘኛ ግጥም መማሪያ መጽሐፍት
- ሪትም ከክፍል 1 እስከ 9

የእስልምና ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍት፡-

- የእስልምና መሠረቶች፡ ከክፍል 1 እስከ 8 + የእስልምና መጀመሪያ እና መዋዕለ ህፃናት-መጀመሪያ

የማኅበራዊ ጥናቶች መማሪያ መጽሐፍት፡-

- የዓለም ታሪኮች፡ ከክፍል 1 እስከ 6
- ሴቶች እና የእስልምና ሕግ

ዓለም አቀፍ አከፋፋዮች፡-
አል-ሙታናቢ መጽሐፍ ቤት፣ ዱባይ፣
የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ

ስዕላዊ መግለጫ፡- ሲዛር ቦቴ

ንድፍ እና አቀማመጥ፡- ፊውቸርን ፕራይም፣ ዱባይ

- የመጀመሪያ እትም፡ 1996
- ሁለተኛ እትም፡ 1997
- ሦስተኛ እትም፡ 2010



አሳታሚ

- አል-አስር አሳታሚ
- ኢሜል፡ salabbhai@emirates.net እና dawood@mutanabbi.com

መቅድም

ይህ የጀማሪዎች የእስልምና መጽሐፍ ለመረዳት ቀላል ፣ ሳቢ እና ማራኪ በሆነ አቀራረብ ተዘጋጅቷል። ይህ የጀማሪዎች መጽሐፍ ተማሪዎች ሁሉንም የእስልምና ሁኔታዎች እንዲያዩ እና እንደ አንድ የህይወት መንገድ እንዲቀበሉ ይረዳል። እስልምና በህይወት ላይ ያለውን ተዕእኖ በጠቅላላ ያሳያል።

መጽሐፉ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ህይወታቸው ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ መመሪያ ነው። በተለያዩ ደረጃ እና የህይወት እርከን ላይ ላሉ ልጆች የትክክለኛ ባህሪ እና ስብዕና መመሪያ ነው። ይህ መጽሐፍ የተማሪዎችን ባህሪ ያስተካክላል። በትምህርት ህይወታቸው ጥሩ ጓደኛቸው ሊያደርጉት እንደሚችሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህ መጽሐፍ የአድርግ እና አታድርግ ትዕዛዞች የሚቀርቡበት ብቻ አይደለም። ባህርያቶችን እና ልማዶችን ያስተካክላል ጥሩና በጎ ስብዕናን የሚገነቡ ትምህርቶችን አጠቃሎ ይዟል። ለአስተማሪዎች እና ለወላጆች ጥሩ የማስተማሪያ መጽሐፍ ነው።

የዚህ መጽሐፍ ስኬት የሚወሰነው በአስተማሪዎች እና በወላጆች እያንዳንዱን ሃሳብ በጥልቀት ከተማሪዎች ጋር በመወያየት መረዳታቸውን ፣ መቀበላቸውን እና መፈፀማቸውን በማረጋገጥ ነው። የመማር ማስተማር ሂደቱ ማወቅን ፣ መረዳት ፣ መቀበል እና በሃሳቡ ላይ መስራት ወይም መፈፀምን ያጠቃልላል። የእያንዳንዱ እውነታ መንፈስ እና መልዕክት በልጆች ስብዕና ላይ ተዕእኖ ሊኖረው ይገባል። እንዲሁም በእለት ተእለት ህይወታቸው ሃሳቡን ወደ ተግባር መቀየር ይኖርባቸዋል።

ኒውደሊ ህንድ ታህሳስ 1997

ሳፊያ ኢቅባል

ለመምህራን

የዚህ መጽሐፍ አላማ ከአምስት እስከ ስድስት አመት እድሜ ላሉ ልጆች የተለመዱ የእስልምና ቃላቶችን ፣ መሰረታዊ ሃሳቦችን እና የግብረገብ ትምህርቶችን ቀለል ባለ መልኩ እንዲገነዘቡ ማስቻል ነው።

ከስድስት እድሜ በታች ላሉ ልጆች በደንብ ማንበብ ላይችሉ ይችላሉ። ሆኖም ይህ መጽሐፍ ትንሽ ፅሁፎችን እና ብዙ ምስሎች ያሉት ሲሆን በመምህራኑ እና በወላጆች ቃላዊ አቀራረብ ላይ የተመሰረተ ነው። እያንዳንዱን ገፅ እንደ አንድ ትምህርት እና ስለአንዷ አረፍተነገር ወይም ሃሳብ ብዙ ማሰራት ይመከራል።

መጽሐፉ ለእያንዳንዱ ቃል በጥያቄና መልስ መልክ ሶስት ትምህርቶችን ይዟል። እነዚህ ትምህርቶች እና ጥያቄዎች ወደ ትምህርት ሊቀየርና ፣ ተያያዥ ሲሆኑ ታሪኮች ሊደገፍ ይገባል። ቀለል ባለመልኩ ስለአንዱ ጥያቄ አንድ ሙሉ ክፍለ ጊዜ ይወያዩበት። ጥያቄና መልሱን በክፍለ ጊዜው መጨረሻ 10 ደቂቃዎች ውስጥ ጥቁር ሰሌዳው ላይ አስፍሩት።

ልጆች አሻንጉሊቶችን ፣ ብሩህ ቀለማትን ፣ አበቦችን ፣ ጣፋጭ ነገሮችን እና የተለያዩ ጨዋታዎችን ይወዳሉ። አዳዲስ ነገሮችን ማየት እና መስራት ፣ አዳዲስ ጨዋታዎችን መጫወት ይወዳሉ። እነዚህን ፍላጎቶች እና የልጆች ዝንባሌ ለማስተማር ልትጠቀሙበት ይገባል። በእያንዳንዱ ትምህርት አሻንጉሊቶችን ፣ ደስ የሚሉ ቻርቶችን ፣ አበቦችን ፣ ጣፋጭ ፍራፍሬዎችን ፣ ጨዋታዎችን ፣ አዳዲስ ነገሮችን ፣ አዳዲስ የማስተማር ዘዴዎችን እነደማስተማሪያ መርጃነት ተጠቀሙባቸው። በእያንዳንዱ ትምህርት አንድ መርጃ መሳሪያ መጠቀማችሁን እርግጠኛ ሁኑ። የማስተማራችሁ ስኬት ማረጋገጫ ይሆናል።

ደስ የሚሉ የሚያብለጨልጩ ፣ ያጌጡ ቻርቶችን ለትምህርቶቹ ጥሩ ቃላቶችን በትልቅ ፊደላት አዘጋጅታችሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አንጠልጥሉት፡፡ ልጆች አበቦችን ይወዳሉ፡፡ ትልቅ አበቦችን ሳሉ እና ልክ አሏህ ፣ ነብዩ ሙሐመድ እንደሚሉ ያሉ ቃላቶችን ከአበቦቹ መሃል ፃፏቸው፡፡

በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ስላለው ሃሳብ መርጃ መሳሪያዎች በመጠቀም ከልጆች ጋር ከተወያያችሁ በኋላ ትምህርቱን ግልፅ እና ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡት፡፡ ከዚያም እንደዚያው ልጆች እንዲያገቡ አድርጉ፡፡ ልጆች ሳይገባቸው ፣ ሳይረዱ እንዳያልፉት ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

የእስልምና ጥናት ክፍለጊዜያቸውን ደስ የሚል በደስታና በጉጉት የሚጠብቁት ክፍለጊዜ እንደሆን የቻላችሁትን ሁሉ አድርጉ፡፡ የተግባር ልምምድ ፈፀሙ በውስጡም የጫዋታ ጊዜ እንዲኖር አድርጉ፡፡ ስለ እናት ሐዲስ ስታስተምሩ የስጦታ ካርድ ከአበባ ጋር አዘጋጅታችሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እያንዳንዱ ልጆች ለወላጆቹ ስጦታውን እንዲሰጡ አድርጉ፡፡ የእስልምና ጥናት ክፍለ ጊዜ መሆን ያለበት ከእረፍት ጊዜ በፊት ነው፡፡ የእረፍት ጊዜ ለልጆች የደስታ የጨዋታ ጊዜ ነው፡፡ የእስልምና ጥናትን ከዚያ ጋር ማያያዝ ደስ የሚል የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ያስችላል፡፡

የጽሁፍ የቤት ስራ ወይም ማስታወሻ ደብተር ሊኖር አይገባም፡፡ ፈተና ሊሰጣቸው የሚገባው የቃል ፈተና ብቻ ነው፡፡

መጽሐፍ የተዘጋጀው ትምህርቶቹን በሶስት ክፍሎች በመክፈል ነው፡፡ እያንዳንዱ ትምህርት የሚበቃው በጥያቄና መልስ ነው፡፡

የፎቶ ምስሎች እና አጫጭር ቪዲዮችን ለመማር መስተማር ሚሚያነት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡ በእሱ መተካት ግን አያስፈልግም፡፡ ለምሳሌ

ካዕባ ስለሚለው ቃል ስታስተምሩ ለ3 ወይም ለአምስት ደቂቃ ለሚሆን ጊዜ የካባ እና የሐጅ ቪድዮ ልታሳዩ ችላላችሁ።።


ውድ መምህር እና ወላጆች ልጆች የሚያዩትን ነገር ኮፒ ስለሚያደርጉ በመጀመሪያ ለልጆቻችሁ እራሳችሁን ሞዴል አድርጉ።። ልጆች የሚያዩት ነገር በቀላል እና ወዲያውኑ ስለሚይዙ ልማዶችን ፣ ባህሪያት እና ያነጋገር እና ያረማመድ ስታይላችሁን ላይ ጥንቃቄ አድርጉ።። ስለሆነም ይህን የልጆች ዝንባሌ በመጠቀም ለእራሳችሁ ተጠቀሙበት እነሱ ኮፒ እንዲያደርጉ እራሳችሁን በጎ ምሳሌ አድርጉላቸው።።

የምታስተምሩትን ግብረገብ እና መልካም ባህሪ እንዲፈፅሙ አድርጉ።።

ሁሉንም ስራ በዚህ ንግግር እንጀምራለን

بِسْمِ ا للهِ الرَّحْمٰنِ الرَّحِيْمِ

ቢስሚላሂ አርረህማኒ አርሂም



በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

እኔ አህመድ ነኝ



አሰሳው አለይኩም

አሰላሙ አለይኩም



ወሕዝቤኩም ኣሕላኽ

ከሊማ /ሸሃዳ

لَآ اِلٰـــــهَ اِلَّا اللّٰهُ


مُحَمَّدُ رَّسُوْلُ اللّٰه

ላ ኢላሃ ኢለሏህ
መሐመደ ረሱሉሏህ

ከአሏህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም

ሙሐመድ የአሏህ መልዕክተኛ ናቸው።

ለሊማውን የማነበው ከመተኛቴ በፊት ነው።




የምተኛውም ቀደም ብየ ነው።

የምተኛው በቀኝ ጎኔ ቀኝ እጀን ጉንጬ ላይ አድርጌ ነው።




ጠዋት የምነሳው በማለዳ ቀደም ብየ ነው።



ከሊማውን ከእንቅልፌም ስነቃ አነባለሁ።

ምስሎቹን አዛምዱ



ሁሉንም የፈጠራቸው አሏህ ነው!

ሐኒሀ

የፈጠረኝ አሏህ ነው!

እነዚህን አበቦች የፈጠራቸው አላህ ነው።

እነዚህን ቢራቢሮዎችም የፈጠራቸው አላህ ነው።




ድመትን የፈጠረው አላህ ነው።



አላህ ሁሉንም ነገር ፈጥሯል።


اللهُ خَالِقُ




አሏህ አል-ሐሊቅ (ፈጣሪው)
ነው።።

اللهُ رَبِّي

አሏሁ ረቢ
ጌታየ አሏህ ነው።።






ነብዩ ሙሐመድ የአላህ ነብይ ናቸው።

ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም

አሏህን እወዳለሁ።።

ነብዩ ሙሐመድንም እወዳለሁ




ቁርአን የአላህ መፅሐፍ ነው።



ሙስሊም


እኔ ሙስሊም ነኝ




ሃይማኖቴ እስልምና ነው።

ተክቢር

አሏሁ አክበር





ስራመድ አልሮጥም። የምራመደው በጥንቃቄ ነው። ጠንከር ያሉ እርምጃዎችን እራመዳለሁ። የምራመደው በእግረኛ መንገድ ላይ ነው። ወደትምህርት ቤት ስሄድ አሮጥም።

ከመብላቴ በፊት እጆቼን እታጠባለሁ። ከመብላቴ በፊትም ቢስሚላህ (በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው እላለሁ) ምግቤን በደንብ እበላለሁ።

بِسْمِ ا للهِ الرَّحْمٰنِ الرَّحِيْمِ



ውሃ የምጠጣው ቀስ ብየነው። የምጠጣው በሶስት ትንፋሽ ነው። ከመጠጣቴ በፊት ግን ቢስሚላህ እላለሁ።



ከጠጣሁ በኋላ ደግሞ አልሐምዱሊላህ እላለሁ።

ከበላሁ በኋላ ይህን ዱአ አደርጋለሁ።

اَلْحَمْدُ لِلّٰهِ الَّذِيْ أَطْعَمَنَا

وَسَقَانَا وَجَعَلَنَا مِنَ الْمُسْلِمِيْنَ



‹‹አልሐምዱሊላሂ ለዚ አጥአምና ወሰቃና
ወጀአልና ሚነል ሙስሊሚን››


እውቀትን የሚፈልግ ሰው የሚያደርገው ዱአ



« ረቢ ዚድኒ ዒልማ »

ሰዎችን ማመስገን ስትፈልጉ በዚህ ቃል አመስግኑ

ጀዛከላህ



አላህ መልካም ነገር ይስጥህ

ምስጋና ለአሏህ



ምስጋና ለአሏህ

ምስጋና ለአሏህ ውዱ አባቴን ለሰጠኝ

ተመስገን ጌታየ እንባየን ለምታብስልኝ አዛኟ እናቴ

ተመስገን ጌታየ ለአበቦቹም


ተመስገን ጌታየ ሰማያዊ ለሆነውም ሰማይ

ተመስገን ጌታየ ላሉኝ አሻንጉሊቶቼ

ተመስገን ጌታየ ላለኝ ነገር ሁሉ


ሁሉም ሙስሊሞች ወንድማማቾች ናቸው።

ሁሉም ሙስሊሞች እኩል ናቸው።




በአለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች ሁሉ
ወንድማማቾች ናቸው።

እንሰሳፉስን



የሰልፉንም መስመር አልሰብርም። መስመሩ ቀጥ ያለ ነው።




ወደ ክፍል ስገባ ‹‹እባክሥ መምህር መግባት እችላለሁ›› እላለሁ።

ወይም ደግሞ በምክኒያት ረፍዶብኝ ከሆነ ይቅርታ ጠይቄ አንድ ታስገባኝ እጠይቃታለሁ።

ሰላላት ይቅርታ እጠይቃለሁ።።





መምህሬን አከብራለሁ እታዘዛለሁ። እወዳታለሁም።


እሷም ትወደኛለች።

ሁሉንም የጥናት ጊዜ ከመጀመራችን በፊት እንዲህ እንላለን

አኡዙቢላሂ ሚነሽይጧኒ ረጅም ቢስሚላሂ ረህማኒ ረሂም

أَعُوْذُ بِا للّٰهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيْمِ

بِسْــمِ ا للّٰهِ الرَّحْـمٰـنِ الرَّحِـــيْم



ከተረገመው ሸይጧን በአላህ እጠበቃለሁ። በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

ክስካ

ጥያቄ፡ አንተ ማነህ ምንድን ነህ?

መልስ፡ ሙስሊም ነኝ

ጥያቄ፡ የፈጠረህ ማነው?

መልስ፡ የፈጠረኝ አላህ ነው።

ጥያቄ፡ ሁሉንም ነገር የፈጠረው ማነው?

መልስ፡ ሁሉንም ነገር የፈጠረው አላህ ነው

ጥያቄ፡ አላህ ማነው?

መልስ፡ አላህ ፈጣሪያችን ነው?

ጥያቄ፡ አላህ አንድ ነውን?

መልስ፡ አዎ! አላህ አንድ ነው።

ጥያቄ፡ አላህ የት ነው?

መልስ፡ አላህ ከሰማያት በላይ ነው። ነገርግን ለእኛ በጣም ቅርብ ነው።

ጥያቄ፡ ሃይማኖትህ ምንድን ነው?

መልስ፡ ኢስላም

ጥያቄ፡ የሆነ ሰው ስታገኝ ምንድን ነው የምትለው?

መልስ፡ አሰላሙ አለይኩም

ጥያቄ፡ የሆነ ሰው አሰላሙ አለይኩም ቢልህ ምን ብለህ ትመልሳለህ?

መልስ፡ ወአለይኩም አሰላም

ጥያቄ፡ አሰላሙ አለይኩም ካልክ በኋላ ምን ትላለህ?

መልስ፡ እነዴት ነህ

ጥያቄ፡ የሆነ ሰው እንዴት ነህ ቢላችሁ ምን ትላላችሁ?

መልስ፡ አልሐምዱሊላህ

ጥያቄ፡ ሰዎችን ለማመስገን የምትሉት ምነድን ነው?

መልስ፡ ጀዛከላህ

ጥያቄ፡ አላህን ታመሰግናላችሁ?

መልስ፡ አዎ ለሁሉም ስጦታዎቹ ሁሉ አላህን አመሰግናለሁ።

ጥያቄ፡ ከሊማዋን አንብቡ?

መልስ፡ ላኢላሃ ኢለላህ ሙሐመድ ረሱሉላህ

ጥያቄ፡ ነብዩ ሙሐመድ ማናቸው?

መልስ፡ ነብዩ ሙሐመድ የአላህ ነብይ ናቸው።

ጥያቄ፡ ማንኛውንም ነገር ከመስራታችሁ በፊት ምን ትላላችሁ?

መልስ፡ ቢስሚላህ

ጥያቄ፡ ከመተኛታችሁ በፊት እና ከተነሳችሁ በኋላ የምታነቡት ምንደነው?

መልስ፡ ከሊማውን

ጥያቄ፡ ቁርአን ምንድን ነው?

መልስ፡ ቁርአን የአሏህ መጽሐፍ ነው።

ጥያቄ፡ ቁርአን የተሰጠው ለማን ነው?

መልስ፡ ለነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)

ጥያቄ፡ ተክቢር በሉ?

መልስ፡ አሏሁ አክበር

ጥያቄ፡ የምትራመዱት እንዴት ነው?

መልስ፡ የምራመደው በጥንቃቄ ነው፤ አልሮጥም። የምንዘው በእግረኛ መንገድ ላይ ነው።

ጥያቄ፡ ከመብላታችሁ በፊት ምን ታደርጋላችሁ?

መልስ፡ እጆቼን እታጠባለሁ። ከመብላቴ በፊት ቢስሚላህ እላለሁ።

ጥያቄ፡ ውሃ የምትጠቱት እንዴት ነው?

መልስ፡ ውሃ የምጠጣው በሶስት ትንፋሽ በጥቂት በጥቂቱ ነው።

ጥያቄ፡ ምግብ ከበላችሁ በኋላ የምታደርጉት ዱአ ምንድን ነው? ፈልጋችሁ አግኙ

ጥያቄ፡ እውቀትን ለማግኘት የምታደርጉት ዱአ ምንድን ነው? ፈልጋችሁ አግኙ

ጥያቄ፡ ወደ መማሪያ ክፍል ከመግባታችሁ በፊት የምትሉት ምንድን ነው?

መልስ፡ እባክዎ መምህር መግባት እችላለሁ

ጥያቄ፡ ሁሉም ሙስሊሞች እኩል ናቸው?

መልስ፡ አዎ ሁሉም ሙስሊሞች እኩል ናቸው።

ጥያቄ፡ ስህተት ስትሰሩ ምንድን ነው?

መልስ፡ የምትሉት ይቅርታ

ጥያቄ፡ መምህራችሁን ትወዳላችሁ? ትታዘዛላችሁ?

መልስ፡ አዎ መምህራችንን እንወዳለን አንታዘዛለንም።

ጥያቄ፡ መምህራችሁ ትወዳችኋለች?

መልስ፡ አዎት ወደናለች

ጥያቄ፡ ከእያንዳንዱ የጥናት ክፍለ ጊዜ በፊት የምታደርጉት ዱአ ምንድን ነው?


መልስ፡ ዱአውን ፈለረጋችሁ አግኙ

ሶላት




ሁላችነም የምንሰግደው ለአሏህ ነው። ሶላት ማለት ስግደት ነው።

እንስሳዎች እና አዕዋፍትም ይሰግዳሉ፡፡ ሁሉም ለአላህ ይሰግዳሉ፡፡




የረመዷንን ወር እፆማለሁ።



ይህን ቃል ቀለም ቀቡ


ሰውም (ፀም)

ካዕባ ቂብላየ (አቅጣጫየ) ነው።



ካዕባ

ሐጅ ለማድረግ ወደ ካዕባ እንሄዳለን።



ዘካ



ድሆችን እንረዳለን።

ገንዘብ እንሰጣቸዋለን።

ዘካ እንሰጣቸዋለን።



ከቤት ወጥቼ ስሄድ ይሄን ዱአ አነባለሁ፡፡

بِسْمِ ا للهِ تَوَكَّلْتُ عَلىٰ ا للهِ

لَا حَـوْلَ وَلَا قُـوَّةَ اِلَّا بِا للهِ


ቢስሚላህ ተወከልቱ አለላህ ወላ ሃውለውላ ቅወተ ኢላ ቢላህ

በአላህ ስም በእሱ ተመካሁ፤ ሃይልም ብልሃትም የለም ከአላህ ቢሆን እንጅ፡፡

ምሽት ላይ አልወጣም

የሚከተሉት ቃላቶች ከከረሚላው ላይ ፃፏቸውና ቀለም ቀቡ

አሏህ ፣ ሶላት ፣ ዘካ ፣ ሰውም ፣ ሐጅ



ጠቃሚ ቃላቶች

ቢስሚላህ

አሏሁአክበር

አል-ሐምዱ ሊላህ

ላ ኢላሃ ኢለሏህ

አሏህ

ሱብሃን አሏህ

ማሻ አላህ

ጀዛከላህ

ነብዩ ሙሐመድ

አሰላሙ አለይኩም

ሶላት

ዘካ

ቀም

ሐጅ

ሐዲስ

ኢማን

አስተግፈሩኟህ

ፊ አማኒላህ

ዱዓ

رَبَّنَـــا اٰتِنَـــا فِي الدُّنْيَـــا

حَسَـــنَةً وَّفِي الْاٰخِـــرَةِ

حَسَنَةً وَّقِنَا عَذَابَ النَّـارِ

ረበና አቲና ፊዱንያ ሃሰነተን ወፊል አሂረቲ ሃሰነተን ወቂና አዛበ ናር።

ትርጉም፡ ጌታችን ሆይ! በዱንያም በአሂራም መልካምን ነገር ስጠን፤ ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።

ይህን ዱአ ሁልጊዜ ከቤቴና ትምህርት ቤት ውስጥ ሆኜ አነባለው።

እውነትን እናገራለሁ!



አላህ ውሸት የሚናገሩ ሰዎችን አይወድም።

ክፍል

ጥያቄ፡ ሶላት ምንድን ነው?

መልስ፡ ሶላት ማለት ለአላህ መስገድ ነው።

ጥያቄ፡ አላህን የምናወራው እንዴት ነው?

መልስ፡ አላህን የምናወራው በሶላት ነው።

ጥያቄ፡ አላህ የሚያወራን እንዴት ነው?

መልስ፡ አላህ የሚያወራን በቁርአን ነው።

ጥያቄ፡ ሁሉም ነገር ለአላህ ይሰግዳል?

መልስ፡ አዎ

ጥያቄ፡ ሰውም ምንድ ነው?

መልስ፡ ሰውም ማለት ፆም ነው።

ጥያቄ፡ ቂብላ ምንድን ነው?

መልስ፡ ቂብላ የምንሰግድበት አቅጣጫ ነው።

ጥያቄ፡ የኛ ቂብላ የትኛው ነው?

ጥያቄ፡ ሐጅ ለማድረግ የምንሄደው የት ነው?

መልስ፡ ሐጅ ለማድረግ የምንሄደው ወደ ካዕባ ነው።።

ጥያቄ፡ ዘካ ምንድን ነው?

መልስ፡ ዘካ ድሆችን ለመርዳት የምንሰጠው ገንዘብ ነው።።

ጥያቄ፡ ከቤት ወጥታችሁ ከመሄዳችሁ በፊት የምታደርጉት ዱአ የትኛው ነው? ፈልጋችሁ አግኙት

ጥያቄ፡ እንዴት ነው የምትራመዱት?

መልስ፡ የማወራው ረጋ ቀስ ብየና ግልጽ ሆኜ ነው።። ሳወራ አልጮህም።።

ጥያቄ፡ ስታነጥስ ምነድን ነው የምትለው?

መልስ፡ አል-ሐምዱሊላህ

ጥያቄ፡ የሆነ ሰው ሲያነጥስ ምንድን የምትለው?

መልስ፡ የርሃሙ ከላ.ህ

ጥያቄ፡ ሁልጊዜ ከትምህርት ቤታችሁና ከቤታችሁ ሆናችሁ የምታነቡት ዱአ ምንድን ነው?

ጥያቄ፡ ብቸኛው ፈጣሪያችን እና አምላካችን ማነው?

መልስ፡ አላ.ህ

ጥያቄ፡ ልናስደስተው የሚገባ ማነው?

መልስ፡ አላህ ብቻ ነው

ጥያቄ፡ ነብዩ ማነው?

መልስ፡ ነብዩ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው።

ጥያቄ፡ የመጀመሪያው ነብይ ማነው?

መልስ፡ ነብዩ አደም (ዐ.ሰ) ነው።

ጥያቄ፡ የመጨረሻው ነብይ ማነው?

መልስ፡ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)

ጥያቄ፡ መልአክቶች እነማንናቸው?

መልስ፡ መልአክቶች የአላህ አገልጋዮች ባሮች ናቸው።

ጥያቄ፡ ቁርአን ከአላህ ተልኮ ወደ ነብዩ ሙሐመድ ይዞላቸው የመጣው ማነው?

መልስ፡ መልአኩ ጅብሪል

ጥያቄ፡ አንድ መልአክ አምላክ መሆን ይችላል?

መልስ፡ አይችልም

ጥያቄ፡ አንድ መልአክ አምላክ መሆን ይችላል?

መልስ፡ አይችልም

ጥያቄ፡ አንድ ነብይ አምላክ መሆን ይችላል?

መልስ፡ አይችልም

ጥያቄ፡ አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር አምላክ መሆን ይችላል?

መልስ፡ አይችልም

ጥያቄ፡ እንዴት ንፁህ መሆን ትችላላችሁ?

መልስ፡ ንፁህ መሆን የምንችለው ጥርሳችንን በመፋቅ ፣ ገላችንን በመታጠብ ፣ ጥፍሮቻችንን በመቁረጥ እና ንፁህ ልብሶችን በመልበስ ነው።


ጥያቄ፡ ዩኒፎርሞቻችንን የምናፀዳው እንዴት ነው?

መልስ፡ ዩኒፎርሞቻችንን የምናፀዳው ዘወትር በማጠብ እና በመተኮስ ነው።

ጥያቄ፡ እውነትን ትናገራላችሁ?

መልስ፡ አዎ እውነትን እንናገራለን።

ሸሃዳ



አሸሃዱ አላ ኢላሃ ኢለላ፧ህ ወአሸሃዱ አነ መ፦ሐመደን ረሱሉላ፧ህ

<u>ትርጉም</u>፡ ከአላ፧ህ ውጭ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እና መ፦ሐመድ የአላ፧ህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡

ԽԼԱՍ ԿԱՊՄ

بِسْمِ اللّٰهِ الرَّحْمٰنِ الرَّحِيْمِ

قُلْ هُوَ اللّٰهُ اَحَدٌ ۚ ①

اَللّٰهُ الصَّمَدُ ۚ ②

لَمْ يَلِدْ ۙ وَلَمْ يُوْلَدْ ۙ ③

وَلَمْ يَكُنْ لَّهٗ كُفُوًا اَحَدٌ ع ④

ሱረቱ ፋቲሃ

بِسْمِ اللّٰهِ الرَّحْمٰنِ الرَّحِيْمِ ۝

اَلْحَمْدُ لِلّٰهِ رَبِّ الْعٰلَمِيْنَ ۝١ الرَّحْمٰنِ
الرَّحِيْمِ ۝٢ مٰلِكِ يَوْمِ الدِّيْنِ ۝٣
اِيَّاكَ نَعْبُدُ وَاِيَّاكَ نَسْتَعِيْنُ ۝٤
اِهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيْمَ ۝٥ صِرَاطَ
الَّذِيْنَ اَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ ۙ غَيْرِ
الْمَغْضُوْبِ عَلَيْهِمْ وَلَا الضَّآلِّيْنَ ۝٧

ሐዲስ



ሐዲስ ማለት የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር እና ተግባር ነው።



ሐዲስ

ጀነት ከእናታችሁ እግር ስር ናት።



እናቴን እወዳታለሁ።


ሐዲስ

ሶላት ብርሃን ናት።



ወደ መስጅድ ስገባ ይህን ዱአ አነባለሁ፡፡

አላሁመ አፍታህ ሊ አብዋበ ረህመቲክ



ሐዲስ

ንፅህና የኢማን ግማሽ ነው።



ንፁህ ነኝ።

ሐዲስ

ልጆች የጀነት አበቦች ናቸው።



ልጆች መልካሞች ናቸው።

ክስሓ

ጥያቄ፡ የሸሃዳ ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ፡ ሸሃዳ ማለት ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም ብሎ መመስከር እና ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር ነው።።

ጥያቄ፡ የሸሃዳ ከሊማ (ንግግር) ፃፉ?

መልስ፡ አሸሃዱ አላ ኢላሃ ኢለላህ ወአሸሃዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉላህ

ጥያቄ፡ ሱራ ኢህላስ አንብቡ?

ጥያቄ፡ ሱራ አልፋቲሃን አንብቡ?

ጥያቄ፡ ሐዲስ ማለት ምንድን ነው?

መልስ፡ ሐዲስ የነብዩ ሙሐመድ ንግግር ነው።።

ጥያቄ፡ አንድ ሐዲስ ስለ እናት ተናገሩ?

መልስ፡ ጀነት ከእናታችሁ እግር ስር ናት።።

ጥያቄ፡ ስለ ንፅህና አንድ ሐዲስ አንብቡ?

መልስ፡ ንፅህና የኢማን ግማሽ ነው

ጥያቄ፡ ስለ ሶላት አንድ ሐዲስ አንብቡ ተናገሩ?

መልስ፡ ሶላት ብርሃን ናት፡፡

ጥያቄ፡ ወደ መስጅድ ስትገቡ የምታነቡት ዱአ ምንድን ነው?

መልስ፡ አላሁመ አፍታህሊ አብዋበ ረህመቲክ

ጥያቄ፡ ስለ ልጆች አንድ ሐዲስ አንብቡ?

መልስ፡ ልጆች የጀነት አበቦች ናቸው፡፡

ጥያቄ፡ ምን አይነት ጓደኞች አላችሁ?

መልስ፡ መልካም ጓደኞች ብቻ

ጥያቄ፡ የእስልምና ትርጉም ምንድን ነው?

መልስ፡ አላህን በመታዘዝ የሚገኝ ሰላም ነው፡፡

ጥያቄ፡ የምትሰግዱት ለማን ነው?

መልስ፡ የምንሰግደው ለአላህ ብቻ ነው፡፡

ጥያቄ፡ ሽርክ ምንድን ነው?

መልስ፡ ሽርክ ማለት ከአላህ ውጭ ላሉ ነገሮች መስገድ ፣ ማጎብደድ እና ለአላህ አጋር ማበጀት ነው፡፡

ጥያቄ፡ አላህን የምትታዘዙት ለምንድን ነው?

መልስ፡ አላህን የምንታዘዘው የእሱን ውዴታ ለማግኘት ፣ ደስታን ፣ ስኬት እና ሰላምን ለማግኘት ነው።

ጥያቄ፡ አላህን የምትታዘዙት እንዴት ነው?

መልስ፡ ቁርአን እና ሱና በመከተል

ጥያቄ፡ ሱና ምንድን ነው?

መልስ፡ ሱና ማለት የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት መንገድ ነው።

ጥያቄ፡ አላህ እሱን እንድንታዘዝ ያስገድደናል? አያስገድደንም?

መልስ፡ አላህ የፈጠረን ማንኛችን መልካም ፣ ማኝኛችን ክፉ እንደሆን ሊፈትነን ነው።

ጥያቄ፡ ጥሩ ነህ ወይስ መጥፎ?

መልስ፡ ጥሩ ልጅ ነኝ።

ጥያቄ፡ በህይወት የመኖራችን አላማ ምንድን ነው?

መልስ፡ የመኖራችን አላማ አላህ እንዳዘዘን መኖር እና እሱን ማስደሰት ነው።

ጥያቄ፡ አምስቱ የእስልምና መሰረቶች ምንድን ናቸው?

መልስ፡ ሸሃዳ ፣ ሶላት ፣ ፆም ፣ ዘካ እና ሐጅ ናቸው።